# አጭር መግለጫ

ማህበራዊ የመገናኛ አውታር/ሚዲያ ትምህርት እና መማርን ለማጎልበት ትልቅ መሣሪያ ሊሆን ይችላል። የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ተማሪዎችን፣ ወላጆቻቸውን /ሞግዚቶቻቸውን፣ እና ማህበረሰቡን በማሳተፍ የእኛን ተልዕኮ እና ዋና ዋና እሴቶቻችንን ለማስፈጸም ሊረዳ ይችላል። ይህንን ጠቃሚ መገልገያ ስንጠቀምበት፣ የ (MCPS) ሠራተኞች በማህበራዊ የመገናኛ አውታር/ሚዲያ የሚናገሩት ወይም ድርጊታቸው እንደባለሙያዎች ሁላችንንም የሚነካ/የሚመለከት መሆኑን ማስታወስ ይኖርብናል። MCPS ሠራተኞቹን መልካም የዲጂታል ዜጎች ምሳሌ እንዲሆኑ ይጠብቃል።

በማህበራዊ የመገናኛ አውታር እንቅስቃሴ ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ለመሣተፍ እንዲረዳዎት እነዚህ ምርጥ የሆኑ ተሞክሮዎች ተዘጋጅተዋል። በየጊዜው እየተለወጠ የሚሄደውን የማህበራዊ መገናኛ/ሚዲያ ገፅታን ለማንጸባረቅ በየዓመቱ ይሻሻላሉ። MCPS ባስቀመጠው የሠራተኛ ስነምግባር ደንብ/Employee Code of Conduct ፣ እና ሌሎችም የ MCPS ህጎች እና ደንቦች/መመሪያዎች እንደ Regulation IGT-RA፣ የመሣሰሉ ስለኮምፒውተር ሲስተሞች፣ ስለኤሌክትሮኒክ ኢንፎርሜሽን፣ እና የኔትዎርክ ደህንነት የተጠቃሚ ኃላፊነቶች፣ እና በአጠቃላይ ተፈጻሚነት ያላቸው የፌደራል እና የስቴት ህጎች፣ እና የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎች መሠረት ላይ ይገነባሉ። እነዚህ ተፈላጊ ነገሮች/መስፈርቶች በጥቅሉ እንደ የ MCPS ህጎች/ደንቦች ይጠቀሳሉ።

የ MCPS ህጎች ተፈጻሚነታቸው በመስመር ላይ/online እንዲሁም በት/ቤቶቻችን እና በስራ ቦታዎች ሁሉ ነው። እንደማንኛውም ሌሎች የሥራ እንቅስቃሴዎች፣ ከተማሪዎች ጋር፣ ወላጆች/ሞግዚቶች፣ ከሥራ ባልደረቦች፣ እና ከማህበረሰቡ ጋር ጨዋነትና ታማኝነት የተሞላበት ሙያዊ አቀራረብ እንዲኖረን ከሁላችንም ይጠበቃል። በመገናኛ አውታርም ሆነ በመማሪያ ክፍል፣ ሠራተኞች ከሚከተሉት ከማናቸውም ድርጊቶች መቆጠብ አለባቸው፦

- የተማሪዎችን፣ የሥራ ባልደረቦችን ወይም የአጠቃላይ ማህበረሰቡን ደህንነት የሚያሰጋ፤
- የሠራተኞችን የሙያ/ፕሮፌሽናል ተአማኒነት የሚያኮስስ፤ እና/ወይም
- የተሰጣቸውን ሥራ ለመፈጸም ብቁ እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል።

## ማህበራዊ መገናኛ አውታር/ሚዲያ ምንድነው?

ማህበራዊ መገናኛ/ሚዲያ ማለት ማናቸውም እርስ በርስ የሚያሳትፍ ድረ-ገጽ ላይ የተመሠረተ ወይም ተንቀሳቃሽ ቴክኖሎጂ ነው። የጋራ ማህበራዊ መገናኛ አውታር/ሚዲያ መድረኮች የሚያካትቱት፦

- Blogs (WordPress, Blogger, Tumblr, etc.)

- የማህበራዊ አውታረ-መረብ ገፆች ፌስቡክ፣ ትዊተር፣ ሊንክደን፣ ወ.ዘ.ተ (Facebook, Twitter, LinkedIn, etc.)
- ፎቶ፣ የተቀረጸ ድምፅ እና ቪዲዮ መላላኪያ ገፆች ዩቲዩብ፣ ቪሚኦ፣ ፍሊከር፣ እንስታግራም፣ ስናፕቻት፣ ሳውንድክላውድ፣ ወ.ዘ.ተ (YouTube, Vimeo, Flickr, Instagram, Snapchat, SoundCloud, etc.)
- ማህበራዊ ቡክማርኪንግ ገፆች ፒንተረስት፣ ረዲት፣ ወ.ዘ.ተ (Pinterest, Reddit, etc.)
- እንደ Wikis አመቺ፣ በግልጽ አርትዕ ሊደረግ የሚችል ይዘት፣እንደ Wikipedia ዓይነት (collaborative, openly editable content, such as Wikipedia)

ሌሎች የተለመዱ የኤሌክትሮኒክ መገናኛ መሣሪያዎች የሚያካትቱት፦ መስመር/ኦንላይን መድረኮች፣ የመልክት አፕስ፣ እና ቴክስት መልክቶች። እነዚህ መገልገያዎች የማህበራዊ ሚዲያ/መገናኛ ካለመሆናቸውም በላይ፣ በእነርሱም ላይ ተመሣሳይ ህግ ተግባራዊ እንደሚደረግ መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

## የሥራ/ሙያዊ ማህበራዊ ሚዲያ ከግል ማህበራዊ ሚዲያ ጋር ሲነፃፀር




የሥራ/የሙያ ማህበራዊ መገናኛ አውታር ከሥራ ጋር የተገናኘና ከት/ቤት ማህበረሰብ ጋር ለመገናኘት ስራ ላይ የሚዉል ነው። የሥራ/የሙያ አካውንቶች እና አውታረ-ስፍራው መቋቋም/መሠራት ያለባቸው በስራ ኢ-ሜይል አድራሻ ነው።

የግል ማህበራዊ ሚዲያ/መገናኛ ከሥራ ጋር የሚገናኝ አይደለም። ለምሳሌ፦ ከጓደኞች ጋር ወይም ከቤተሰብ ጋር ለመገናኘት ትጠቀሙበት ይሆናል። የግል ማህበራዊ መገናኛ አውታር አካውንቶች እና አውታረ-ስፍራው መቋቋም/መሠራት ያለባቸው በግል ኢ-ሜይል አድራሻ ነው።

የግል ማህበራዊ መገናኛ እንቅስቃሴዎች ሥራችሁ ላይ ተፅእኖ ለማሳደር እንደሚችሉ በአእምሮ መያዝ ያስፈልጋል። የ MCPS ሠራተኞች የግል ህይወታቸውን እንቅስቃሴ (የማህበራዊ ግንኙነት/ሚዲያን አጠቃቀምን ጨምሮ) የ MCPS ስራ ላይ ውጤታማነታቸውን በማይጎዳ ሁኔታ እንዲጠቀሙ ይጠበቃል። ማናቸውም ወንጀል ነክ የሆኑ ነገሮች፣ ታማኝነትን ማጉደል፣ ወይም ሌላ ተገቢ ያልሆኑ እንቅስቃሴዎች በ MCPS ሥራችሁ ላይ ተቃራኒ/ጎጂ ውጤት ሊያስከትል ይችላል። የበለጠ ኢንፎርሜሽን ለማግኘት ቀጥሎ ያሉትን መረጃዎች ይመልከቱ፦ article

22F of the MCAAP agreement, article 11A of the MCEA agreement, and article 35C of the SEIU agreement.

---

## ፍንጭ፡- በማህበራዊ ሚዲያ መደረግ የሌለባቸው ነገሮች

ባለጌ፣ ፀያፍ፣ ትህትና የሌለው፣ ተልካሻ/መናኛ፣ መረን፣ብልግና/ነውር፣ ዘርን የሚያዋርድ/የሚያጎድፍና ዘረኝነትን የሚያባብስ፣ ስም የሚያጠፋ/ዝናን የሚያጎድፍ፣ የሚያስከፋ/አፀያፊ፣ የፆታ/የዘር ጥቃት/ትንኮሳ፣ ወይም ነውረኛ፣ የብልግና ቃሎችን በሚያስተጋቡ ባህርያት አትሳተፍ(ፊ)።

ጠብ/ጭቅጭቅ ውስጥ አትሳተፍ(ፊ) ወይም ለጥቃት የሚጋብዝ አስተያየት ላይ ምላሽ አትስጥ(ጪ)። ስለ አስተያየት ወይም ስለ ተጠቃሚው(ዋ) የሚያሳስብህ(ሽ) ከሆነ የኮሙኒኬሽን መምሪያን አግኝ (ኚ)።

በመረጃ ያልተደገፉ የሃሜት ወሬዎችን/ጭምጭምታ ፖስት አታድርግ/ጊ ወይንም አታስተላለፍ/ፊ።

በስራው ላይ በይፋ ተመድበህ (ሽ)በት ካልሆነ በስተቀር የ MCPS ወይም የት/ቤት ቃልአቀባይ አድርገህ(ሽ) ራስህ(ሽ)ን አታቅርብ/ቢ።

ማንም አያውቀኝም ብለህ/ሽ አትገምት/ቺ።

ወላጆቻቸው ወይም ሞግዚቶቻቸው በጽሑፍ ፈቃድ ሰጥተው ካልሆነ በስተቀር በክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን ምስል አትለጥፍ(ፊ)/ፖስት አታድርግ(ጊ)። ስለ ተማሪ ገመና/privacy ተጨማሪ መረጃ/ኢንፎርሜሽን በ Annual Notification for Directory Information and Student Privacy/ ስለ ተማሪ ገመና/privacy መመሪያ ዓመታዊ ማስታወቂያ ላይ ይገኛል።

በግል ማህበረሰብ ሚዲያ ገጾች ላይ ስለተማሪዎች ፎተግራፎችን ወይም ቪዲዮ ወይም ማንኛውንም መረጃ/ኢንፎርሜሽን አትጠቀም/አትጠቀሚ።

ለማየት የሚያስቸግር/ጥራት የሌላቸው ምስሎች ወይም ቪዲዮዎች ለምሳሌ፡- በጣም የደበዘዙ ምን እየተደረገ እንደሆነ ለማረጋገጥ አስቸጋሪ የሚሆኑ ምስሎችን- ወይም የግልህን/የግልሽን ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ፖስት የተደረገ ሁኔታ ፖስት አታድርግ/ጊ።

# ፍንጭ፡- የምትለጥፈው(የምትለጥፊው)/ፖስት የምታደርገ(ጊ)ው ፋይዳ እንዲኖረው ስለማድረግ

## ሚዛናዊ አመለካከትን ተጠቀም(ሚ)

ስትለጥፍ/ፖስት ስታደርግ(ጊ) ምንም እንኳ ተመሣሣይ ምላሽ ባይሰጡም ሁልጊዜም ስለሌሎች አስተያየትና አመለካከት ያለህ(ሽ)ን አክብሮት አሳይ። ከአርእስት ውጪ ወይም የሚያናድዱ አስተያየቶችን ማስወገድ።

## ከመለጠፍህ(ሽ)/ፖስት ከማድረግህ(ሽ) በፊት አስብ(ቢ)

እውነት ነው? ጠቃሚ ነገር ነው? አስፈላጊነትስ አለው? የሚያጓጓ ነው?

## ታማኝ እና እውነተኛ ሁን/ኚ

## ፊደሎችንና ሰዋሰው/ግራመሩን በደንብ ፈትሽ/ሺ

## ተገቢውን እውቅና ስጥ/ስጪ

ከሌሎች ሰዎች ማቴሪያል ጋር የሚገናኝ ነገር ስትጠቀም(ሚ)/ስትጠቅስ(ሺ) ተገቢውን ዋጋ እውቅና መስጠት ያስፈልጋል።

## Hyperlinks ሃይፐርጠቋሚ መገናኛ ትሮችን መፈተሽ/Check Hyperlinks

አገናኝ የተለጠፈው/ፖስት የተደረገው hyperlink መሄድ ወዳለበት እንደሄደና የመልክቱ ይዘትም ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጥ/ጪ።

## ለሌሎች የእውቀት/የክህሎት ባለቤትነት አክብሮት ስጥ(ጪ)

ተገቢ ፈቃድ ያልተሰጠህ(ሽ) ከሆነ ሌሎች ያቀረቡትን ሠነድ ወይም ቪድዮ በሙዚቃ የታጀበ ወይም ሙዚቃ፣ ወይም የስነጥበብ ሥራ/ስዕል አትለጥፍ(ፊ)/ፖስት አታድርግ/ጊ። ለምሳሌ፡- አንድ ነገር ለግል አገልግሎት ገዙት ማለት በአውታረ-መረብ ላይ ሊያቀርቡት መብት አለዎት ማለት አይደለም።

## በግል አካውንት ላይ፣ የእርስዎ አመለካከት የእራስዎ ብቻ መሆኑን መግለጽ

አንዳንድ ምሳሌዎችን ለመጥቀስ፡- "አመለካከቶቹ የራሴ ናቸው"፣ "አስተያየቶቹ የግሌ ናቸው"፣ እና "የኔ አመለካከቶች ናቸው"።

### በመደበኛነት/Regularly ለጥፍ(ፊ)/ፖስት አድርግ(ጊ)።

አዲስ ነገር የሚጠብቁ ካልሆነ በስተቀር ተጠቃሚዎች ተከታይ የመሆን ምክንያት አይኖራቸውም።

### የት/ቤት ማህበረሰብ ድጋፍ

ይደሰቱ፣ ችሎታዎን ያጋሩ፣ ጥሩ ዜናን ያጋሩ፣ ጠቃሚ መረጃዎችን እና እይታዎችን ያቅርቡ፣ እና ለጭውውቱ ዋጋ የሚያሰጥ እሴት ያክሉ

### የትምህርቱን/የጉዳዩን ማቴሪያል በጥልቀት ተመልከት/ቺ

የተማሪ መታወቂያ ወይም ውጤት የመሣሰሉ ነገሮች፣ ለሌሎች ማካፈል/ማሳየት የሌለብህ/የሌለብሽ የተማሪ መረጃ/ኢንፎርሜሽን በአንተ/ቺ ፎቶ ወይም ቪድዮ ላይ አለ? ተማሪዎች-ወይም ማንም ቢሆን በፎቶ ወይም ቪዲዮ ላይ እንደ አሳፋሪ ነገር ሊታሰብ የሚችል ወይም የሚያንቋሽሽ/የሚያዋርድ/የሚያጥላላ ነገር አለበት?

### በጣም ጥሩ የሆነውን የተስተካከለ አይነት ፎቶ/ቪድዮ ምረጥ/ጪ

በሚጠቀሙበት መድረክ ላይ የትኛው የፎቶ እና የቪዲዮ አቀማመጥ የተሻለ እንደሚመስል ይረዱ/ይገንዘቡ። ለምሣሌ፡- አግዳሚ ፎቶዎች በ Facebook እና Twitter ላይ በደንብ ይታያሉ።

# ለሥራ/ሙያዊ ማህበራዊ መገናኛ/ሚድያ ምርጥ ተሞክሮዎች

## ከታሰበበት ግብ ለመድረስ ትክክለኛውን የማህበራዊ መገናኛ አውታር/ሚዲያ መድረክ (Platform) መምረጥ

የምትጠቀሙባቸውን የማህበራዊ መገናኛ አውታር ምንጮችና አካውንቶችን/social media sites and accounts ዓላማ እና ህጎቹን ማወቅና ማህበራዊ የመገናኛ አውታር አካውንት በመክፈት ለማከናወን የምትፈልገው/የምትፈልጊው ግልፅ የሆነ ግብ እንዲኖርህ(ሽ) ያስፈልጋል።

### የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS ) የሙያ/የሥራ/ professional ሚዲያ አካውንቶች ጥቅም ላይ መዋል ያለባቸው ለትምህርት ዓላማ ብቻ ነው፣ ይኼውም፡-



1. በቀጥታ የትምህርት ስርጭትን፣ ማስተማርን፣ አስተዳደራዊ፣ የቢዝነስ እና/ወይም የድጋፍ አገልግሎቶችን የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ MCPS ተልእኮን የሚያራምዱ/የሚያስተዋዉቁ ተግባራትን የሚያካትት፣ እና



2. ከማናቸውም ማስተማር፣ ፕሮጀክት፣ ሥራ፣ የተሰጠ ሥራ፣ተጠቃሚው(ዋ) ኃላፊነት ለተጣለበት ተግባር ወይም ክንዉን ጋር የተገናኘ።



በማህበራዊ መገናኛ አውታር/ሚዲያ ለመሳተፍ ስታስቡ፣ ግባችሁን ለመድረስ የትኛው የሚድያ መድረክ የበለጠ/በላቀ ደረጃ ሊረዳችሁ እንደሚችል ጭምር መታሰብ አለበት። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ MCPS የ myMCPS parent/student portal እና ጉግል አፐስ/ Google Apps ለትምህርት፣በነዚህም ላይ ጨምሮ፣ በርካታ የመስመር ላይ መገልገያዎችን ያቀርባል። ከክፍል ተማሪዎች እና ከወላጆቻቸው ጋር ለመገናኘት የ MCPS መገልገያ ካለ አስፈላጊ ሲሆን ብቻ መጠቀም እንደሚያስፈልግ ይጠበቃል። የተለየ አይነት አቀራረብ በሚረጋገጥ ደረጃ ካስፈለገ ብቻ የ MCPS ያልሆነ መገልገያ ተጠቀም/ሚ። ለምሳሌ:- መምህራን ክፍል ውስጥ ከተማሪዎቻቸው ጋር ለመገናኘት ቢፈልጉ፣ የተገኘውን/ያለውን የ MCPS መገልገያ መጠቀም አለባቸው። ከሰፊው የት/ቤት ማህበረሰብ ጋር ወይም አውታረ-መረብ ላይ ከሙያቸው ጋር የተገናኘ ተሳትፎ ለማድረግ ከሆነ ሌሎች/የውጭ ማህበራዊ የመገናኛ-መረብ እንደ ቲዊተር ወይም ፌስቡክ ለመጠቀም መሠረት ይኖረዋል። ወይም ለምሳሌ:- አንድ የአትሌቲክስ አሰልጣኝ ውጤቶችን ከጨዋታ ስፍራ ለሰፊው የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ለማስተላለፍ ቢፈልግ/ብትፈልግ፣ እንደ ትዊተር ወይም ፌስቡክ ለመጠቀም መሠረት አለው። እርስዎ ምን ዓይነት መገልገያዎችን/tools ለማግኘት እንደሚችሉ ለማረጋገጥ፣ እንዲረዳዎት፣ የቴክኖሎጂ ዲፖርትመንት የኢንትግሬሽን እና ድጋፍ ክፍልን/Department of Technology Integration and Support ያግኙ።

## ለሱፐርቫይዘሮች እና ለወላጆች/ሞግዚቶች ማሳወቅ

የ MCPS ሠራተኞች ከሥራ ጋር የተገናኘ ማህበራዊ ሚዲያ አካውንት ከመክፈታቸው አስቀድመው ለሱፐርቫይዘራቸው ማሳወቅ አለባቸው። በተጨማሪ፣ ቀደም ሲል ሪፖርት ያልተደረገ ማናቸውም አይነት ለሥራ የሚውል ማህበራዊ ሚዲያ መገልገያ ካለ ለሱፐርቫይዘር ማሳወቅ ያስፈልጋል። ለሚያስተላልፉት፣ ለሚጭኑት፣ እና አውታረ-መረብ ላይ እንዲገኝ ለሚያደርጓቸው ነገሮች በሙሉ ኃላፊነቱ የግልዎ መሆኑን እባክዎ ያስታውሱ። በተጨማሪ፦ ለሙያ ሥራ ማህበራዊ አውታረ-መረብ አጠቃቀም ሠራተኞች የሚጠብቁት ውስን የሆነ የግል ገመና እንደሚሆን እባክዎ ያስታውሱ።

ሠራተኛው(ዋ) በት/ቤት ወይም በዲፓርትመንት ደረጃ አካውንት መስርቶ/ታ ወይም እንዲመሰረት ጠይቆ/ቃ ከሆነ የመግቢያ ሚስጥር መረጃዎቹን ርእሰ መምህር ወይም ሱፐርቫይዘር ጭምር እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። የሙያ ማህበራዊ አውታረ-መረብ/ሚዲያ አካውንት ያላቸው ሱፐርቫይዘሮች የሠራተኞቻቸውን የሥራ አካውንት እንዲከተሉ ይደፋፈራሉ።

የ MCPS ሱፐርቫይዘሮች እና ሌሎችም ኃላፊነት ያላቸው የ MCPS ሠራተኞች የሥራ ማህበራዊ አውታረ-መረቦችን እና የድረ-ገጽ እንቅስቃሴዎችን ኦዲት/ምርመራ የማድረግ መብት አላቸው። በተጨማሪ፣ የ MCPS ሱፐርቫይዘሮች ልጥፎችን/posts እና/ወይም አካውንቶቹን የ MCPSን ህግ ወይንም ደንብ የማይጠብቁ ከሆነ እንዲሰረዙ መጠየቅ ይችላሉ፤የ MCPSን ህግ ወይም ደንቦች በማይጠብቁ ሠራተኞች ላይ በየደረጃዉ የዲስፕሊን እርምጃ ሊወሰድባቸው ይችላል።

ልጆቻቸው እንዲሳተፉ የሚጠየቁበት ማናቸውም አዲስ ማህበራዊ የመገናኛ አውታረ-መረብ ሲኖር ለተማሪዎች ወላጆች/ሞግዚቶች በቅድሚያ መነገር አለበት። ይህ ማስታወቂያ ት/ቤቶች ከቤተሰቦች ጋር ስለ ክፍል ትምህርት እና ስለት/ቤት እንቅስቃሴዎች በሚያስተላልፉበት ተመሣሣይ ሁኔታ መነገር አለበት ሠራተኞችም እንደዚሁ ልጆች በስንት ዓመት እድሜ ለመጠቀም እንደሚችሉ/እንደሚፈቀድ የማህበራዊ መገናኛ አውታረ-መረብ/ሚዲያ ደንቦችን ማንበብ አለባቸው።

## ለሥራ/የሙያ  የማህበራዊ መገናኛ አውታር አካውንት መክፈት/ማቀናጀት

ለሥራ ጉዳይ የማህበራዊ መገናኛ አውታር አካውንት ለመክፈት ሁልጊዜ የMCPS ኢ-ሜይል አድራሻ ይጠቀሙ። የግል ኢ-ሜይል አድራሻዎን በፍጹም አይጠቀሙ። የ MCPS ሠራተኞች ለሥራ የሚጠቀሙት ማናቸውም የማህበራዊ መገናኛ አውታረ-መረብ ከግል አካውንታቸው የተለየ መሆኑን በግልጽ ቋንቋ መቀመጡን እርግጠኞች መሆን አለባቸው። እርስዎ የሚሠሩበት መምሪያ፣ ጽ/ቤት፣ ወይም ት/ቤት የማህበራዊ መገናኛ አውታረ-መረብ ያለው ከሆነ፣ የሚጽፈው(የሚለጥፈው)/posting ግለሰብ ስም ከማድረግ ይልቅ የመምሪያው፣ የጽ/ቤት፣ ወይም የት/ቤት ስም የተገልጋዩ/የተጠቃሚ  ስም (username) እና/ወይም መያዣ አካል መሆን አለበት። የግል ማህበራዊ

መገናኛ አውታረ-መረብ አካውንት ካለዎት አካውንቱ የራስዎ መሆኑን እና እርስዎ MCPSን ወክለው እየተናገሩ አለመሆንዎን ግልጽ ማድረግ አለብዎት። አሁን በሥራ ላይ ያለው የማህበራዊ መገናኛ አውታረ-መረብ ስም ወይም መገለጫዎች የሥራ መሆኑን የማይገልፅ ከሆነ በተቻለ ፍጥነት መሻሻል አለበት። ስለአካውንቱ መግለጫ ታክሎበት ያለ ለምሳሌ፡-የ Instagram አካውንት ስያሜው @mrjohnson_tenthgradeclass, "Created by Mr. Johnson/Posts are my own" የሚል ከሆነ ተቀባይነት ይኖረዋል። ነገር ግን ስያሜው @samjohnson የሚል ዓይነት የ Instagram አካውንት፤ ተጠቃሚውን የ Mr. Johnson's የግል Instagram አካውንት እንደሆነ አድርጎ እንዲያምን/እንድታምን ሊመራ ይችላል። ተጨማሪ መመሪያ ካስፈለገዎት፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ኮሚኒኬሽንስ ዲፓርትመንትን/MCPS Department of Communications ያነጋግሩ።

የሙያዊ/ሥራ ማህበራዊ አውታረ መረብ ሚዲያ አካውንት/Media Account ተገቢ/ትክክለኛ ስም፡-

@mrjohnson_tenthgradeclass

@samjohnson

## የማህበራዊ አውታረመረብ አካውንቶችን ገመና እና ደህንነት መጠበቅ

ሠራተኞች ስለሚጠቀሙባቸው የማህበራዊ መገናኛ አውታረ-መረቦች ህጎችን፣ ስያሜዎችን እና የብትሕውነት አደረጃጀቶች/ቅንብሮች የማወቅ/የመረዳት ኃላፊነት አለባቸው። የሥራ ማህበራዊ መገናኛ አውታር አካውንቶች ላይ አግባብነት ያላቸው የግላዊነት/ብትሕውነት አደረጃጀቶች/ቅንብሮች ጥቅም ላይ መዋል አለባቸዉ። ይሁን እንጂ፣ አውታረ-መረብ ላይ ምንም ነገር በእውነተኝነት የግል እንዳልሆነ ያስተዉሉ። ምንም እንኳ በግል የመጠቀም ሁኔታ የተስተካከለ ቢሆንም፣ የእርስዎን የግል ጉዳይ-ሚስጥር እንዲመለከት የተፈቀደለ(ላ)ት ማንኛውም ሰው ቅጂ/ኮፒ አድርጎ(ጋ) መለጠፍ እና ለሌላ ሰው ማስተላለፍ ይችላል/ትችላለች። መረጃውን/ኢንፎርሜሽኑን ቢሠርዝቱም እንኳ ለረዥም ጊዜ በድረ-ገጽ ሰርቨሩ/website's server ላይ ሊቆይ ይችላል።

እርስዎ የሚጠቀሙባቸውን ማህበራዊ ሚዲያ ደህንነት የመጠበቅ ኃላፊነትም አለብዎት፣ እና በእርስዎ አካውንት ወይም የይለፍ ቃል/password or account ለሚፈጸሙ ለማናቸውም ነገሮች/ድርጊቶች ሙሉ ኃላፊነት አለብዎት። ጠንካራ የሆነ የይለፍ ቃሎችን/strong passwords በመፍጠር መከላከል እንዳለብዎት ያረጋግጡ፣ ያልተፈቀደለት ሰው የእርስዎን የይለፍ ቃል/passwords ወይም በእርስዎ አካውንት ተጠቅሞ/ተጠቅማ ከሆነ፣ ወይም ማንኛውንም ለድረገጹ ደህንነት የተጣሰ ሁኔታ ወዲያውኑ ለሱፐርቫይዘር ማሳወቅ አለብዎት፤ በተጨማሪም ሥራዎን ባጠናቀቁበት ጊዜ ሁሉ የእርስዎን አካውንት መዝጋት አለብዎት።

## ማህበራዊ መገናኛ አውታረ-መረብ ላይ ማስታወቅ/መለጠፍ/Posting to Social Media

ከሥራ ጋር የተገናኙ አካውንቶቻችሁን ለማሳደስ የ MCPS ኮምፒውተሮችን ወይም ሌሎች ፕሮፌሽናል መገልገያዎችን እንድትጠቀሙ እናደፋፍራለን። በማህበራዊ የመገናኛ አውታረ-መረብ ላይ ከማሳወቅ/መለጠፍ አስቀድሞ በትክክል ማመዛዘን አለብዎት። ለሥራ የማህበራዊ መገናኛ አውታሮችን አካውንት ልክ እንደሥራ ቦታዎ ተቀጣይ አድርገው መያዝ አለብዎት። የሌሎች ሠራተኞች፣ ወላጆች/ሞግዚቶች፣ እና ሌሎች በት/ቤት ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን ልዩ ልዩ አስተያየቶችና እምነቶችን ከበሬታ መስጠት ያስፈልጋል። እርስዎ የለጠፉት/ፖስት ያደረጉት ነገር በዋሽንግተን ፖስት/Washington Post ጋዜጣ የመጀመሪያ ገጽ ላይ ታትሞ ቢወጣ ወይም በዋሽንግተን ፖስት ድረ-ገጽ ላይ፣ ወይም ያለእርስዎ እውቅና በሁሉም ዘንድ የተነዛ/የተሰራጨ ቢሆን ምን ሊሰማዎት እንደሚችል ይገምቱ። የሌሎችን ይዘት በሚያጋሩበት ጊዜ ተመሣሣይ ህግ እንደሚተገበር እንዳይዘነጉ፣ መልሶ ትዊት ማድረግና አገናኞችን ለሌሎች ማጋራትን ጨምሮ፣ ስለዚህ ምን እንደሚያጋሩ ሲወስኑ በጥንቃቄ ማሰብ ያስፈልጋል።

ማናቸውንም በሥራ ምክንያት የሚያገኟቸውን ሚስጥራዊ መረጃዎች/ኢንፎርሜሽን፣ ስለተማሪዎች ወይም ስለወላጆቻቸው የሚታወቁ መረጃዎችንና በግል የተቀዱ ነገሮችን በማህበራዊ መገናኛ አውታር ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የ MCPS ሠራተኞች እንዳያጋልጡ የተከለከለ ነው።

ምን ያህል በተደጋጋሚ ፖስት እንደሚያደርጉ ያስቡ። የማህበራዊ መገናኛ አውታር አካውንቶችን ወቅታዊ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሳለ፣ ሁልጊዜ የሚለጥፉ/ፖስት የሚያደርጉ ከሆነ፣ ሥራዎን በውጤታማነት ይሠሩታል?

የተማሪዎችን ገመና ለመጠበቅ፣ የMCPS ሠራተኞች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪዎችን በየግላቸው የሚያሳዩ ምስሎችን እንዳይለጥፉ/ፖስት እንዳያደርጉ ማስወገድ አለባቸው። ለምሳሌ፡- የተማሪን እጆች ወይም በስተጀርባ ጭንቅላታቸውን መጠቀም በክፍል ውስጥ የሚካሄድ እንቅስቃሴ ስዕላዊ መግለጫ ለመስጠት ይረዳል። በስፖርት እንቅስቃሴ ላይ እያሉ ከሆነ ወይም ሌሎች ለት/ቤት ማህበረሰብ ክፍት የሆኑ ዝግጅቶች ከሆኑ የተማሪን ፊት የሚያሳይ ቪዲዮ ወይም ፎቶ የበለጠ ተገቢ ነው፣ ቢሆንም ግን ምን ፖስት እንደሚያደርጉ/እንደሚለጥፉ እና ስለተማሪው/ዋ ገመና ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ከተጠራጠሩ ይጠይቁ። በተጨማሪ፣ አንዳንድ ሰዎች ደስተኞች ስለማይሆኑ የሥራ ባልደረቦችን ፎቶ መገናኛ አውታር ላይ ከመለጠፍ/ፖስት ከማድረግ አስቀድሞ ፈቃድ መጠየቅ አስፈላጊ ነው።

በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ተለይተው የሚታወቁበትን ዓይነት ምስሎች ከመለጠፍ/ፖስት ከማድረግ ይቆጠቡ፡፡

የ MCPS ሠራተኞች አስቀድሞ ከሚመለከታቸው ግለሰቦች ፈቃድ ካላገኙ በስተቀር የ MCPS ተማሪዎችን፣ ወላጆችን/ሞግዚቶችን፣ የሌሎች ሠራተኞችን፣ የበጎ ፈቃድ አገልጋዮችን፣ ወይም ኮንትራክተሮችን ፎቶ መለጠፍ/ማንጠልጠል የለባቸውም። የ MCPS ሰራተኞች ለፎቶዎች መለያ ወይም መግለጫ ሲሰጡ የተወሰኑ የተማሪዎች ብዛት (ለምሳሌ:- የልዩ ትምህርት ተማሪዎች) ለይቶ ማቅረብ የለባቸውም። ከ MCPS ድረ-ገጾች/የመገናኛ አውታሮች ተወስደው የሚለጠፉ/ፖስት የሚደረጉ ነገሮችን MCPS ከማናቸውም ማህበራዊ መገናኛ አውታር የማስወገድ/የመከልከል መብቱ የተጠበቀ ነው።

## ልዩ ትኩረት የሚያሻቸው ነገሮች ምሳሌዎች



ሁልጊዜም ያስታውሱ ጠቅላላ የMCPS የሠራተኞች ስነ-ምግባር ደምብ በማህበራዊ የመገናኛ አውታር አጠቃቀምዎ ሁኔታም ተፈፃሚነት ይኖረዋል፣ ነገር ግን አውታረ መረብ ላይ ፖስት ከማድረግዎ በፊት አንዳንድ ምሳሌዎች ላይ ትኩረት መስጠት አለበት።

- የተማሪዎችን፣ የሠራተኞችን፣ የወላጆችን/ሞግዚቶችን፣ ወይም የሕዝብን ደህንነት አደጋ ላይ በሚጥል ወይም በሚያሰጋ ሁኔታ ውስጥ አትሳተፍ/አትሳተፊ።
- በተማሪዎች፣ ወላጆች/ሞግዚቶች፣ የስራ ባልደረቦች፣ ሱፐርቫይዘሮች፣ ወይም ሌሎች ዜጎች ላይ በዘር፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በዝርያ፣ በብሄራዊ ማንነት፣ በሃይማኖት፣ በስደተኝነት አቋም፣ በፆታ፣ በጾታ ማንነት፣ በፆታ መገለጫ፣ በፆታ ዝንባሌ፣ በቤተሰብ/በወላጆች አቋም፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በእድሜ፣ በአካል/በአእምሮ ስንክልና፣ በድህነት፣ እና በማህበራዊ ኤኮኖሚ አቋም፣ በቋንቋ፣ ወይም ሌሎች በህግ ወይም በህገመንግስት ከለላ የተደረገላቸው ባህሪያት/መለያ ወይም ትስስር ጋር በተገናኙ ሁኔታዎች ምክንያት አድልዎ አታድርግ/አታድርጊ።
- ተማሪዎችን፣ ወላጆችን/ሞግዚቶችን፣ የሥራ ባልደረቦችን፣ ወይም ሌሎች ጎልማሶችን አታስፈራራ/ሪ፣ አታስጨንቅ/ቂ፣ አታዋክብ/ቢ፣ አትተንኩስ/ሺ፣ አትዛት/ቺ፣ አትፈታተን/ኚ።
- ማንኛውንም ልጅ ሆነ ደካማ አዋቂ በማጎሳቆል ወይም በቸልተኝነት አትበድሉ፣ አንድ/ዷት አዋቂ ወይም በስልጣን ላይ የሚ(ምት)ገኝ ለብዝበዛ ወይም ለማጎሳቆል አላማ ከአንድ/ዷት ልጅ ጋር ስሜታዊ ግንኙነት ለመገንባት እና እምነታቸዉን ለማግኘት የመደባበስ/የማባበል ስነምግባርን ጨምሮ።

- የተማሪው/ዋ እድሜ የፈለገውን ያህል ቢሆን፣ ከአንድ የMCPS ተማሪ ጋር የፍቅር ወይም የፆታ ግንኙነት ለማድረግ አትሳተፉ ወይም አትሞክሩ።
- ወሲብ-ነክ ፅሁፍ/ቪድዮ ለMCPS ተማሪዎች አታሳዩ፣ ወይም ልጆችን ከወሲብ-ነክ ሁኔታ ጋር አታገናኙ/አታሳትፉ።
- በMCPS ንብረት ወይም በማንኛውም የMCPS እንቅስቃሴ ወሲብን ለማነሳሳት የታለመ ብልሹ ድርጊት አታስተዋውቁ፣ አታሳዩ፣ ወይም አታሰራጩ።
- ከተማሪዎች ጋር በኢ-ሜይል፣ ማህበራዊ ሚድያ፣ የቴክስት መልእክቶች፣ የመልእክት መተግበርያዎች፣ እና በሌሎች ኤሌክትሮኒክ የመገናኛ መሳርያዎች ከማስተማር ወይም ከMCPS የስራ ሃላፊነታችሁ በቀጥታ ወደተዛመዱ ተገቢ ዓላማዎች ላይ ብቻ መወሰን።
- በማህበራዊ የመገናኛ አውታር (ሶሻል ሚድያ)፣ በኢ-ሜይል፣ በቴክስት መልክቶች፣ በመልክት አስተላላፊ apps፣ ወይም ሌላ የኤሌክትሮኒክስ መገናኛዎች ከትምህርት ጋር በቀጥታ ያልተገናኙ ነገሮችን ወይም ከ MCPS የሥራ ኃላፊነት ጋር ቀጥታ ግንኙነት የሌላቸውን ነገሮች ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪ ጋር የአንድ-ለ-አንድ ግንኙነት አታድርግ/አታድርጊ። ከተማሪዎች ጋር በጊዝያዊ ወይም ስም ሳያስታውቁ በመልእክት መተግበርያዎች ኣማካይነት መገናኘት ክልክል ነው።



- ከተማሪዎች ጋር በኢሜይል መለያዎች፣ በማህበረሰባዊ ሚድያ ኣውታረመረብ ጣብያዎች፣ የፅሁፍ መልእክቶች፣ የመልእክት መተግበርያዎች፣ ወይም በሌሎች መገናኛዎች ኣትገናኙ ወይም "ጓደኞች" ኣትሁኑ።

---

# ሪፖርት ስለማድረግ

የ MCPS ሠራተኞች በማህበራዊ የመገናኛ አውታር የሚታዩ አግባብነት የሌላቸው ሁኔታዎችን ሪፖርት ማድረግ አለባቸው። አንዳንድ ምሣሌዎችን ለመጥቀስ:- ህፃናትን ማጎሣቆል እና ቸልተኝነት፣ ህገወጥ እንቅስቃሴዎች፣ በአውታረመረብ ላይ መተንኮስ/ጭቅጨቃ፣ ዛቻ፣ እና/ወይም ማስፈራራት ከሌላ የ MCPS ሠራተኛ ወይም ከሌላ ግለሰብ የ MCPS ሥራቸውን በሚመለከት ወይም የሚነካ ሁኔታዎችን ያካትታል። በተጨማሪም፣ የሞንትጎመሪ


ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ሠራተኞች (MCPS employees) የተማሪ ጥቃት ከተመለከቱ ስለ ሪፖርት አደራረግ የተቀመጠውን አቅጣጫ ተከትለው ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ስለ ተማሪ ጥቃት፣ ዛቻ፣ ማስፈራራት ደንብ/Regulation JHF-RA, Student Bullying, Intimidation and Harassment።

---

# ከጋዜጦች የሚቀርቡ ጥያቄዎች

በማህበራዊ ሚዲያ ስለ MCPS ጋዜጣዊ መግለጫ ለመስጠት ከተጠየቁ ወደ ኮሙኒኬሽን ዲፓርትመንት/Department of Communications ማሳለፍ/መምራት አለብዎትpio@mcpsmd.org

# የግል ማህበራዊ ግንኙነት አውታረ-መረብ ምርጥ አጠቃቀም



ሠራተኞች ሌላም መተግበር ያለባቸው፤ የግል ማህበራዊ መገናኛ አውታር ሲጠቀሙ ጥንቃቄ እና ጥሩ ሚዛናዊነትን ነው። በዲጂታል ዓለም የሙያ/ፕሮፌሽናል እና የግል መካከል ያለው መስመር ብዙውን ጊዜ የደበዘዘ ነው። በግል አውታረመረብ ላይ ራስዎን እንደ MCPS ሠራተኛ የሚያቀርቡ ከሆነ፣ የራስዎን ማንነት እና ተዛማጅነት ያላቸውን ነገሮች ለሥራ ባልደረቦች፣ ለወላጆች፣ እና ለተማሪዎች ማቅረብ የፈለጉት ይዘታቸው ወጥነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ አለብዎት።

እርስዎ በማህበራዊ የመገናኛ አውታር ላይ የሚያወጡት/ፖስት ያደረጉትን በሥራ ባልደረቦች እና በአብዛኛው ህብረተሰብ ዘንድ ምን ዓይነት ትርጉም ሊኖረው እንደሚችል ያስቡበት። እርስዎ፣ ትምህርት ቤትዎ፣ ወይም ጽ/ቤትዎ (መሥሪያ ቤትዎ) ምን ዓይነት አጠቃላይ ገፅታ እንዲኖራችሁ እንደሚፈልጉ ራስዎን ይጠይቁ።

የግል ማህበራዊ መገናኛ አውታረመረብ መጠቀም በት/ቤት ወይም በሥራ ቦታ እንቅፋት የመፍጠር አቅም እንዳለውና ከ MCPS ደንቦች ጋር የሚፃረር ስለሆነ ተገቢ የዲሲፕሊን እርምጃ የሚያስወስድም ሊሆን ይችላል። ለምሣሌ፦ ሠራተኞች ማስቸገር/መተንኮስ፣ ማስጨነቅ ወይም የሥራ ጓዶችን ወይም ተማሪዎችን በግል ማህበራዊ የመገናኛ አውታር አካውንት ማስፈራራት አይችሉም።

ከተማሪዎች ወይም ከወላጆች ጋር በግል አውታረመረብ ጣብያዎች "ጓደኞች" አትሁኑ ወይም የተማሪዎችን ምስል በግል አካውንት ላይ አትለጥፉ/ፖስት አታድርጉ።

በስራ ቀናት የግል ማህበረሰባዊ መገናኛ አውታር ላይ ፖስት ለማድረግ የ MCPS ን መገናኛ አውታር አትጠቀሙ። በተጨማሪም፤ የ MCPS ሰራተኞች የግል ማህበራዊ ሚዲያ ቦታዎቻቸውን መዳረሻ ለመቆጣጠር ተገቢ የግል/ብትሕውነት ቅንብሮችን/አደረጃጀቶችን እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ።

የ MCPS ሠራተኞች MCPSን ወክለው እንደሚናገሩ በማስመሰል አንባቢው እንዲያምን በግላቸው ማህበረሰባዊ የመገናኛ አውታረ መረብ አካውንት ላይ እንዳይለጥፉ/ፖስት እንዲያደርጉ አይፈቀደም። ይህ እገዳ የሚያካትተው፤

በዚህ አይወሰንም፣ የ MCPS ት/ቤትን ዋና የመለያ ምልክቶች/አርማዎች logos or mascots/ወይም ለ MCPS የተሰጡ ይዘቶችን/ይዞታ ጭምር ነው። ቢሆንም፤ የሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤቶች ዋና መለያ ምልክቶች/MCPS logos ከማህበረሰባዊ የመገናኛ አውታረ መረቦች ጋር በራስ- ሰር የተካተቱ ለምሳሌ እንደ፡- LinkedIn ይፈቀዳሉ።